# በጳጳሳቱ መሰደድ ምክንያት ስለተፈጠረው ችግር የሚነገረውን ስሕተት ለማረም

ጌታቸው ኃይሌ

በብፁዓን ጳጳሳት መሰደድ ምክንያት ስለተፈጠረው የመከፋፈልችግር በብዙ ተጽፏል ። ወደዚያ እንደገና አልሄድም ። ይህን ጽሑፍ ያረቀቅሁት "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ/ቅ/ሲኖዶስ" በሚል ርእስ ተደርሶ በአሲምባ (Assimba) ድረ-ገጽ ላይ ወጥቶ ባየሁት ድርሰት ላይ ያየኋቸውን የእኔን ጽሑፍ ለመቃወም ከተሰነዘሩት ስሕተቶች ዋና ዋናዎቹን ለማረም ብቻ ነው ። ጥቅሱ ውስጥ የፊደል መዘባረቅ ቢታይ የምጠቅሰ ሰነድ ስሕተት እንጂ ፥ የእኔ አይደለም ።

1. <u>ጥቅስ ፤</u> "በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ከባድ ችግር ስለደረሰባት ቤተ ክርስቲያኗ በዓለም ተበትና በስደትና በመከራ ትኖራለች ።" . . . "የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ መቀበሉም መልካም ነዉ ግን እርሱን ከተቀበለ መጀመሪያ ምን አሰደደው?"

   <u>እርማት ፤</u> ይህ ጥቅስ የሚጠቁመው በቤተ ክርስቲያኗ ላይ ከባድ ችግር ስለደረሰ የተሰደዱ ካሉ ፥ እነሱን ነው ። ደጋግሜ እንደተናገርኩት ፥ ኢትዮጵያውያን መሰደድ የጀመሩት ከደርግ ዘመን ጀምሮ በሀገሪቱ ላይ በደረሰው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር ነው ። ስደት የሚያመጣው በቤተ ክርስቲያን ላይ በሚደርስ ከባድ ችግር ብቻ አይደለም ። ለማንኛውም የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ነፃ እንዲሆን መታገል እንጂ ፥ "መቀበሉም መልካም" አይደለም ።

2. <u>ጥቅስ ፤</u> "[የሲኖዶስ ስብሰባ ] ፓትርያርኩ ወይም ሊቀ ጳጳሱ እርሱ በተገኘበት ፣ እርሱ በሚኖርበት ወይም እርሱ በፈቀደበት ቦታ ይሆናል ። ለምሳሌ ፫ቱ ዐበይት ሲኖዶስ የሆኑት የመጀመሪያዉ በኒቅያ ፣ ሁለተኛይቱ በቀኊስጥንጥንያ ፣ ሦስተኛዋ በኤፌሶን ነው የተደረገው ። ፫ቱም በዛሬዉ ቱርክ ግዛት ነዉ ። የዚያን ጊዜ ሊቀ ጳጳስ የነበረዉ የሮሙ ሲሆን እርሱ ባለበት በሮም አልተደረገም ነገር ግን በተፈቀደበት ቦታ ሆኗል ።"

   <u>እርማት ፤</u> የዚያን ጊዜ ሊቀ ጳጳስ የቀኊስጥንጥያው እንጂ ፥ የሮሙ አልነበረም ። ያውም ቢሆን ፥ በዚያን ዘመን ሃይማኖት መንግሥታዊት ስለነበረች ፥ እነዚህ የተጠቀሱት ሲኖዶሶች የተደረጉት ቄሳሩ በፈቀደበት እንጂ ፥ ሊቀጳጳሱ በፈቀደበት ቦታ አልነበረም ። ከቄሳር ዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (284-305 ዓ.እ.) ጀምሮ ፥ የሮም ቄሳራዊ መንግሥት በምሥራቅና በምዕራብ ተከፈለ ። ቈስጠንጢኖስ (306-337 ዓ.እ.) በምሥራቁ መንግሥት ላይ ሲነግሥ ፥ ዋና ከተማነትን ከሮም ወስዶ ለበረንጥያ (ለByzantum) ሰጣት ፤ ስሟም በስሙ "ቊስጥንጥንያ" ፥ አንዳንዴም "አዲሷ ሮማ" ተባለ ። የዚያን ጊዜ የነበረው የሮሙ ሊቀ ጳጳስም የበላይነቱን አብሮ ለቀኊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ አስረከቧል ። የቀኊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ "ዓለም አቀፋዊ ፓትርያርክ" (Ecumenical

Partiarch) የሚባለው እነዚ ዓለም አቀፋዊ ጉባኤዎች በሱ ግዛት ስለተደረጉ ነው ። ቱርክ የሚኖሩ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳት እስከዛሬ "ሩም ርሁባን" ይባላሉ ("የሮም መነኮሳት" ማለት ነው) ። ከተማይቱን የኛ መጻሕፍ ም "ሮም ዘግሪክ" ይሏታል ። ቁም ነገሩ እነዚህ የተጠቀሱት ጉባኤዎች የተደረጉት ቄሳር ቈስጠንጢኖስና ቄሳር ቴዎዶሶስዮስ በነገሡበት በምሥራቁ የሮም ቄሳራዊ መንግሥት (የበራንጥያ መንግሥት) መሆኑን ማስታወስ ነው ። ለዚህ የሚረዳው ቅዱስ ቄርሎስ ለንጉሥ ቴዎደስዮስ "ስለ ርትዕት ፣ ሃይማኖት ፣" እና ለንጉሡ እኅቶች ለአርቃዲያና ለመሪና "ከመ ፣ አሐዱ ፣ ክርስቶስ ፣" (ክርስቶስ አንድ ስለመሆኑ) በመማፀን የጻፈላቸውን ትምህርተ መለኮት መመልከት ይጠቅማል ።

3. <u>ጥቅስ ፤</u> "ቅዱስ ሲኖዶስ በአመት ሁለት ጊዜ እንዲደረግ የቤተ ክርስቲያናች[ን] ሕግ ፍትሐ ነገስቱ እንዲህ ሲል ይናገራል "ሁለተኛ ኒቅ ፯ ። ኒቅ ፤ ፵፰ ። በየቦታው ሁሉ ኤጲስ ቆጶሳት በየዓመቱ ሁለት ጊዜ ከጳጳሳቸዉ ወይም ከሊቀ ጳጳሳቸዉ ዘንድ ይሰብሰቡ ።""

<u>እርማት ፤</u> ጥቅሱ ልክ ነው ፤ ግን "በየቦታው ሁሉ" የሚለው የብዙ ቊጥርና ባለፈው ጽሑፌ የጠቀስኩት የአፄ ዘርአ ያዕቆብ ማብራሪያ እንደሚያሳዩት ፥ ጥቅሱ የሚያመለክተው ስለሀገረ ስብከታዊ <u>ጉባኤዎች</u> እንጂ ፥ ስለማእከላዊው ሲኖዶስ አይደለም ። እኔም ስዱዳን ካህናትን የምማፀነው ፥ ይኸንን ቀኖና ተከትለው ፥ በተገፉት ፓትርያርክ መሪነት እንዲያስተባብሩን ነው ።

4. <u>ጥቅስ ፤</u> "ከልት" ፤ "ከልት" ፤"ከልት" ፤ "አንዳንድ የኛም ወገኖች ይኸን የመሰለውን ሥርዓት አልባ ነት ቤተ ክርስቲያን እያሉ በግላቸው ያቋቁማሉ ።"

<u>እርማት ፤</u> ቃሉን መጀመሪያ ሳየው ፥ "cult" የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል መሆኑ ቶሎ አልገባኝ ነበር ፤ ምክንያቱ ፥ አለቦታው ገብቶ ስላገኘሁት ነው ። ምክንያቱ ም ፥ አምልኳቸው በከልት የሚመሰል የኦርቶዶክስ ኅበረተ ሰብ የትም ከተማ አላየሁም ። ጳጳስ ያላቀሰሰው ቄስ ፥ ጳጳስ ያላዴቆነው ዲያቆን ምናልባት በጴንጠቆስጤዎች "ቸርች" አካባቢ ይገኙ ይሆናል እንጂ ፥ በኦርቶዶክሶዎቹ ኅብረተሰብ ውስጥ የሉም ። ሁሉም "ሐዋርያዊ ትውፊት" የሚከተሉ ናቸው ። እንዲያውም ፥ ብዙ ኅብረተሰቦች ትልቁ ችግራቸው ካህን ማጣትና "እኛ ያቋቋምነውን ማእከላዊ ሲኖዶስ ካልተቀበላችሁ" መባላቸው ነው ። ሐዋርያዊ ጳጳስ ያልቀሰሱ ካህናት የሚያቆርቧቸው ኅብረተሰቦች ካሉ ፥ በሀገር ልጅነት እንጂ ፥ በሃይማኖት "የኛም ወገኖች" አይባሉም ። እርስ በርሱ የሚጋጭ አነጋገር ነው ።

ላሁኑ ጨርሻለሁ ።